የደቡብ ብሔሮች ፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት

# ደቡብ ነጋሪት ጋዜጣ
# DEBUB NEGARIT GAZETA

OF THE SOUTHERN NATIONS, NATIONALITIES AND PEOPLES' REGIONAL STATE

ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፫
አዋሣ—ኅዳር ፫ ቀን ፲፱፻፺፬

የደቡብ ብሔሮች ፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ
መንግሥት ምክር ቤት ተጠባባቂነት የወጣ

7th Year No. 3
AWASSA — 12th November, 2001

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፴፯/፲፱፻፺፬ ዓ.ም
"የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፴፯/፲፱፻፺፬" ........ ገጽ ፩

## CONTENTS

Proclamation No. 37/2001
"Southern Nations, Nationalities and Peoples' Regional State Agricultural Research Institute Proclamation No. 37/2001." ........ Page 1

### አዋጅ ቁጥር ፴፯/፲፱፻፺፬ ዓ.ም
### የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩትን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

ለክልሉ የኢኮኖሚ ልማት መሠረት የሆነውን ግብርናን ይበልጥ ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችል ክልል በቀል የሆነ የግብርና ቴክኖሎጂን ለማሳደግ፣ በሌሎች ክልሎች በፌዴራል ምርምር ማዕከላትና እንዲሁም በውጭ ከሚገኙ የግብርና ምርምር ተቋሞች የሚገኙትን የቴክኖሎጂ ውጤቶች ከክልሉ የግብርና ልማት ፍላጎት ጋር ለማጣጣም በክልል ደረጃ የሚደረግ ምርምር ወሳኝነት ያለው በመሆኑ፤

ከዚህም አንፃር የክልሉ የግብርና ልማት ፍላጎት በተሟላ ሁኔታ እንዲካሄድ የሚያግዝ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን የማፍለቅ፣ የማበልጸግና የማላመድ፣ የማስተባበር፣ የመደገፍና የማበረታታት ኃላፊነት ያለው ራሱን የቻለ አካል ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በክልሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 51፣ ንዑስ አንቀጽ ፫(ሀ) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

#### አንቀጽ ፩

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፴፯/፲፱፻፺፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

#### አንቀጽ ፪

፪· ትርጓሜ

፩· "ክልል" ማለት የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ማለት ነው።

### *PROCLAMATION NO. 37/2001*
### *A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF SOUTHERN NATIONS, NATIONALITIES AND PEOPLES' REGIONAL STATE AGRICULTURAL RESEARCH INSTITUTE*

WHEREAS, it is believed that a regional agricultural research for generating technologies for the region, improving indigenous agricultural technologies of the region, adapting technologies generated in other regional and federal research centres as well as in national and international research institutions in other countries in line with the region's agricultural development strategy is a decisive activity to develop agriculture which forms the basis for the development of the regions's economic development;

WHEREAS, it has become necessary to establish an institution which shall be responsible for generating, improving and adapting technologies and coordinating, encouraging and assisting research activities in order to fulfill the agricultural requirements of the region;

NOW THEREFORE, in accordance with Article 51 section 3(a) of the constitution of the Region, it is here by proclaimed as follows:

#### Article 1

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "Southern Nations, Nationalities and Peoples' Regional State Agricultural Research Institute Proclamation No. 37/2001."

#### Article 2

2. *Definition*

1. "Region" means the Southern Nations, Nationalities and Peoples' region.

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 1.50

ደቡብ ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፲፰
Debub Negarit G.P.O.Box 18

፪· “የግብርና ምርምር” ማለት በዕፅዋት፣ በእንስሳት፣ በግብርና ምጣኔ ሀብት እና በተፈጥሮ ሀበት (ደን፣ አፈር፣ የውሃ ውስጥ ሀብት) ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚከናወን ምርምር ነው።

፫· “ቦርድ” ማለት የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የግብርና ምርምር ቦርድ ማለት ነው።

፬· “ማዕከል” ማለት የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ሥር የተቋቋመ የግብርና ምርምር ማዕከል ማለት ነው።

አንቀጽ ፫

፫· መቋቋም

፩· የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት (ከዚህ በኋላ ኢንስቲትዩት እየተባለ የሚጠራ)፣ የሕግ ሰውነት ያለው፣ ራሱን የቻለ የክልል መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

፪· ኢንስቲትዩቱ ተጠሪነቱ ለክልሉ የግብርና ምርምር ቦርድ እና ለክልሉ የገጠር ልማት ማስተባበሪያ ቢሮ ይሆናል።

አንቀጽ ፬

፬· ዋና መሥሪያ ቤት

የኢንስቲትዩቱ ዋና ጽ/ቤት አዋሣ ይሆናል።

አንቀጽ ፭

፭· ዓላማ

የኢንስቲትዩቱ ዓላማ፦

፩· የክልሉን የዕድገት ስትራቴጂ፣ የግብርና ፖሊሲ እና የተጠቃሚዎችን ፍላጎት መሠረት ያደረጉ ቴክኖሎጂ ዎችን ማፍለቅ፣ ማበልጸግ፣ እና ማላመድ፣

፪· የክልሉ የግብርና ምርምር ፈጣን፣ ውጤታማ እና የልማት ፍላጎትን መሠረት ያደረገ እንዲሆን የሚያስችል አቅም መገንባትና ሥርዓት መዘርጋት፣

፫· የግብርና ምርምር ውጤቶችን እንደአስፈላጊነቱ ከክልሉ ግብርና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ቢሮና ከሌሎች ከሚመለከ ታቸው መ/ቤቶች ጋር በመተባበር ለሕዝብና ለሌሎች ተጠቃሚ አካላት ማስተዋወቅ ናቸው።

አንቀጽ ፮

፮· የኢንስቲትዩቱ ሥልጣንና ተግባር፣

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል ።

፩· የክልሉን የግብርና ልማት ፖሊሲ መሠረት ያደረገ የግብርና ምርምር ስትራቴጂ መንደፍና የአፈጻጸም ቅደም ተከተሉን መወሰን፣ የሥራ ፕሮግራምና ዕቅድ ማውጣት፣ በቦርዱና በክልሉ መስተዳድር ም/ቤት ሲፀድቅ ተግባራዊ ማድረግ፣ እንዲሁም በሚመለከታቸው ክፍሎች ተግባራዊ መሆኑን መከታተል፣

፪· የክልሉን የግብርና ምርምር ፖሊሲ አፈፃፀም መከታተል፣ እንደአስፈላጊነቱ የፖሊሲ ማሻሻያ ሀሳብ ለቦርዱ ማቅረብ፣ በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ሲፀድቅም ተግባራዊ ማድረግ እና መከታተል፣

፫· ከክልሉ የልማት ፍላጎት ጋር የሚጣጣሙ የግብርና ምርምር ዕቅዶችና ፕሮጀክቶች ለመቅረጽና ለማዘጋጀት የሚያስችል መመሪያ ማውጣት፣ እንደአግባቡም ተዘጋ ጅተው የቀረቡ ፕሮጀክቶችንና ዕቅዶችን መገምገምና በመመሪያው መሠረት መዘጋጀታቸውን ማረጋገጥ፣ ለቦርዱ ቀርቦ እንዲፀድቅ ማድረግ፣

፬· የክልሉን ፖሊሲና ስትራቴጂ መሠረት በማድረግ የግብርና ምርምር ማከናወን ወይም እንዲከናወን ማድረግ፣



2. "Agricultural Research" means research undertaking amied at improving the production and productivity of plants, animals and natural resources (forests, Soils, aquatic resources).
3. "Board" means the Southern Nations, Nationalities and Peoples' region Agricultural Research board.
4. Agricultural research Centre" means an agricultural research organ established or to be established or administered by the Southern Nations, Nationalities and Peoples' Regional State Agricultural Research Institute.

Article 3

3. *Establishment*
   1. The Southern Nations, Nationalities and Peoples' Regional State Agricultural Research Institute (hereinafter referred to as "Institute") is hereby established as an autonomous regional body of the Southern Nations, Nationalities and Peoples Regional State.
   2. The Institute shall be accountable to the regional agricultural research board and to the regional rural development coordination bureau.

Article 4

4. *Head office*

   The head office of the Institute shall be in Awassa.

Article 5

5. *Objectives of the Institute*

   The Institute shall:
   1. generate, develop and adapt agricultural technologies that focus on the needs of the over all development strategy, agricultural policy of the region and their beneficiaries;
   2. Build up a research capacity and establish a system that will make the agricultural research of the region efficient, effective and based on development needs;
   3. Populariz agricultural research resulsts among users in collaboration, whenever necessary, with the regional Agriculture and Natural Resources Development Bureau, and other relevant Institutions.

Article 6

6. *Powers and Duties of the Institute*

   The Institute shall have the powers and duties to:
   1. formulate agricultural research strategies and determine research prioperties based on the region's agricultural development policies; develop work plans and programs and implement when approved by the board and the regional government, and follow up the implementation thereof;
   2. follow up the implementation of agricultural research Policy of the region, initiate new and improved policy proposals and submit the same to the board, and when approved by the regional government, implement and follow up the implementation thereof;
   3. issue guidelines for the proper formulation and preparation of agricultural research programs and projects in line with the region"s development requirements; Where appropriate evaluate whether the proposed projects, programs and budget are in accordance with the guidelines and submit them to the board for approval:
   4. Undertake or cause the undertaking of agricultural research activities on the bases of the agricultural research policy and strategy of the region;

፭· ማንኛውም በኢንስቲትዩቱ ሥር የሚተዳደር የግብርና ምርምር ማዕከል እንዲጠናከር ማድረግ፣ እንደአስፈላጊነቱ አዲስ ማዕከላት በተለያዩ ሥነ ምህዳሮች እንዲቋቋሙ ማድረግ፣

፮· አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር ጠቀሜታቸው የተረጋገጠ የግብርና ምርምር ውጤቶችን ተጠቃሚው ክፍል እንዲያውቃቸውና በሥራ ላይ እንዲያውላቸው፣ በክልሉ የግብርና ምርምር ማዕከላትና በተጠቃሚው ሕብረተሰብ መካከል የተቀናጀ አሠራር እንዲኖር የሚያግዝ ሥርዓት መዘርጋትና በተግባር ላይ መዋሉን መከታተል፤

፯· አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የሕብረተሰቡን የግብርና ዕውቀት ለማሳደግ የግብርና ምርምር ውጤቶችን አመቺ በሆኑ የመገናኛ ዘዴዎች በልዩ ልዩ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ቋንቋዎች የማሳወቅ ተግባር ማከናወን፤

፰· በኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ድርጅትና በሌሎች የግብርና ምርምር ማዕከላት እንዲሁም በዓለም አቀፍ የግብርና ምርምር ተቋማት መካከል ሊኖር የሚገባውን የሥራ ግንኙነት አግባብ ካለው የፌዴራልና የክልል መስተዳድር ጋር በመመካከር መወሰን፣ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት በክልሉ ውስጥ በተለያዩ ደረጃ የግብርና ምርምር ከሚያካሄዱ ቢሮዎችና ተቋማት፣ አገር አቀፍ፣ አህጉር አቀፍና ዓለም አቀፍ የግብርና ምርምር ተቋማት ጋር ግንኙነት መመሥረት፣ ማስተባበርና ስምምነቶችን መፈራረም፣ ተግባራዊ ማድረገ ወይም ተግባራዊነታችንን መከታተል፣

፱· በክልል፣ በአገር ውስጥና በውጪ አገር ስለተካሄዱና የሚካሄዱ የግብርና ምርምሮችና ውጤታቸውን የሚመለከቱ መረጃዎችን ማሰባሰብ፣ መተንተን፣ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት መዘርጋት፣

፲· በክልሉ የግብርና ምርምር ላይ የሚሠማራ ብቃት ያለው የሰው ኃይል ለማፍራትና ያለውንም ለማሻሻል በሚደረጉ ጥረቶች ላይ ተሳትፎ ማድረግ፣ በኢንስቲትዩቱ የተሠማራውን የሰው ኃይል አቅም ማሳደግና መገንባት የሚያስችል ስልት መቀየስና ተግባራዊ ማድረግ፣

፲፩· የግብርና ተማራማሪዎች እና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞችን የሚያበረታታ አመቺ የሥራ ሁኔታዎችን መፍጠር፣ ተመራማሪዎችን በተመለከተ በሙያ ላይ የተመሠረተ የዕድገት መሰላል መዘርጋት፣ ማሻሻል፣ በቦርዱም ሲፀድቅም ተግባራዊ ማድረግ፣

፲፪· የክልሉን የግብርና ምርምር በሚመለከቱ ማናቸውም ጉዳዮች ላይ መሳተፍና የክልሉን መንግሥት ማማከር፣

፲፫· በክልሉ ውስጥ በተለያዩ ደረጃዎች ምርምር በሚያካሂዱ ተቋሞች መካከል አስፈላጊ ያልሆኑ የምርምር ፕሮጀክቶች ድግግሞሽና የሀብት መባከን እንዳይኖር ለመከላከል የሚያስችል ሥርዓት አግባብ ካላቸው ተቋማት ጋር በመተባበር መዘርጋት፣

፲፬· በክልሉ ውስጥ በግብርና ምርምር ላይ የተሠማራ ወይም የሚሠማራ ማንኛውም መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት በክልሉ የግብርና ምርምር ስትራቴጂ መሠረት ምርምር ማካሄዱን መከታተልና መቆጣጠር፣ የሥራ ሪፖርትም መቀበል፤ በክልሉ ውስጥ በግብርና ምርምር የተሠማራውን ማንኛውንም ሰው መዝግቦ ዝርዝሩን መያዝ፤

፲፭· የንብረት ባለቤት መሆን፣ ውል መዋዋል፣ መክሰስና መከሰስ፣

5. reorganize any agricultural research center under the Institute and establish new ones in different agroecological zones as deemed necessary;
6. establish a system, in collaboration with appropriate organs, to make effective coordination between agricultural research centres of the region and the end users and implement and follow up the implementation so that useful agricultural research results will be popularized and utilized by the end users;
7. advertise agricultural research results in the languages of the different nations and nationalities using appropriate means in collaboration with relevant organs, in order to widen the agricultural knowledge base of the society.
8. decide the working relations between the Institute and the Ethiopian Agricultural Organization, Agricultural Research Insitutes and Centers of other regions, international Agricultural Research Institutions in consultation with relevant federal and regional government bodies; establish relaitonships, cooperate and conclude agreements with institutions at different administrative levels, national, continental and global institutions having similar objectives, based on the relevant law and implement and follow up the implementation thereof;
9. collect, organize and disseminate information on agricultural research activities and results that are available in the region, country and elsewhere in the world and develop and coordinate information exchange mechanisms;
10. participate in the development and upgrading of human resources that will take part in regional agricultural research; formulate and implement strategies to develop and build up the capacity of human resources of the institute;
11. create suitable working conditions to encourage agricultural researchers and support staff; develop and improve a professional career structure for researchers and implement when approved by the board;
12. participate and advise the regional government in all matters related to agricultural research in the region;
13. establish a system, in cooperation with relevant institutions, to avoid unnessary duplication of research projects and subsequent wastage of resources in different institutions in the region;
14. follow up and supervise the implementation of the regional agricultural research strategy by governmental and non-governmental organziations that undertake agricultural research in the region, and receive reports; register and maintain the list of any person involved in agricultural research in the region;
15. Own properties, enter into agreement, sue and be sued;

፲፮· ዓላማዎቹን ከግብ ለማድረስ አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተዛማጅ ተግባሮችን ማከናወን።

<u>አንቀጽ ፯</u>

፯· <u>የኢንስቲትዩቱ አቋም፤</u>

ኢንስቲትዩቱ፤–

፩· የግብርና ምርምር ቦርድ (ከዚህ በኋላ "ቦርድ" እየተባለ የሚጠራ)፤

፪· በቦርድ አዘጋጅነትና በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር አቅራቢነት በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የሚሾም ዋና ሥራ አስኪያጅ፤

በዋና ሥራ አስኪያጁ አቅራቢነት በቦርዱ የሚሾሙ የምርምር ዳይሬክተሮች፤

፬· በኢንስቲትዩቱ ሥር የተቋቋሙ /አዋሳ፣ አረካ፣ ጂንካ/እና የሚቋቋሙ የግብርና ምርምር ማዕከላት፤

፭· በማዕከል ተመራማሪዎች ተመርጠው በዋና ሥራ አስኪያጅ የሚሾሙ የግብርና ምርመር ማዕከላት ሥ/ አስኪያጅ እና

፮· አስፈላጊ ሠራተኞች ይኖሩታል ።

፰· <u>የቦርዱ አባላት፤</u>

ቦርዱ ሰብሳቢውን ጨምሮ አግባብነት ያላቸውን ቢሮዎች የሚወክሉና በክልሉ መስተዳድር ም/ቤት የሚሰየሙ አባላት ይኖሩታል ።

፱· <u>የቦርዱ ተጠሪነት፤</u>

የብርዱ ተጠሪነት ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ይሆናል።

፲· <u>የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር፤</u>

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩትል ።

፩· በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ ላይ የተዘረዘሩትን የኢንስቲዩቱን ዓላማዎች ያስፈጽማል ።

፪· በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፮ ላይ የተዘረዘሩትን የኢንስቲትዩቱን ሥልጣንና ተግባራት በበላይነት ይመራል ፤ የአዋጁን አፈጻጸም በበላይነት ይቆጣጠራል ፤ ይከታተላል ፤

፫· የክልሉን የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩቱና ማዕከላት መዋቅር መርምሮ ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት አቅርቦ ያስፀድቃል ፤ ሲፈቀድም ሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል ።

፬· የኢንስቲትዩቱ ሠራተኞች የሚተዳደሩበትን ደንብ ያፀድቃል ።

፭· የኢንስቲትዩቱን ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራምና በጀት ይመረምራል ፤ ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ቀርቦ እንዲፀድቅ ያደርጋል ፤

፮· በክልሉ የግብርና ክፍለ ኢኮኖሚ ወሳኝ ሚና ያላቸውን የክልሉን የተለያዩ ሥነ–ምህዳራዊ አካባቢዎችና የግብርና ሥርዓቶች በሚወክሉና ለወደፊቱ እምቅ ሀብት ባላቸው አካባቢዎች የምርምር ማዕከላትን ማቋቋም ሲያስፈልግ የውሳኔ ሀሳብ ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ያቀርባል ፤ የፖሊሲ ጉዳዮችንም መርምሮ ለውሳኔ ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ያቀርባል ።

፯· የቴክኒክ አማካሪ ኮሚቴ ያቋቁማል ፤ አባላቱን ይሰይማል፤ ለሚቀርቡ የምርምር ሀሳቦች ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች በጀት ከመፈቀዱ በፊት የቴክኒክ ግምገማ ሪፖርት ከኮሚቴው ይቀበላል ፤ ይወስናል ፤

፰· የክልሉን የግብርና ምርምር ፤ ኤክስቴንሽንና ገበሬ አገናኝ ም/ቤትን ይገመግማል ፤ የሥራ ሪፖርት ይቀበላል፤

፱· የኢንስቲትዩቱን ዋና ሥራ አስኪያጅ በመምረጥ በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር አቅራቢነት በክልሉ መስተዳድር ም/ቤት እንዲሾም ያደርጋል ፤ የኢንስትዩቱን የምርምር ዳሬክቴሮች ይሰይማል ፤

፲· በምርምር ሥራ ጥሩ ውጤት ያስመዘገቡ ተመራማሪ ዎችን እየገመገመ ማበረታቻ እንዲሰጣቸው ለክልሉ መንግሥት ያቀርባል ፤

16. Accomplish other tasks related to the above in order to fulfill its objectives.

Article 7

7. *Institutional structure*

The Institute shall have:

1. Agricultural research Board (here in after referred to as "Board")
2. A Director General to be appointed by the president of the regional state upon presentation by the Board,
3. Research Dirctors to be appointed by the board upon presentation by the Director General,
4. Agricultural Research Centres established (Awassa, Areka, Jinka) or to be established under the Institute.
5. Center Directors to be appointed by the Director General upon election of candidates by researchers of the respective centers, and
6. The necessary staff

8. *members of the Board*

The Board shall have a chairperson and members who are representing relevant bureaus and will be appointed by the regional government.

9. *Accountability of the Board*

The board shall be accountable to the regional government.

10. *Powers and Duties of the Board*

The Board shall have the power and duties to:

1. overview the objectives of the institute enumerated in Article 5 of this proclamation;
2. direct the powers and duties of the Institute enumerated in Article 6 of the proclamation, and supervise and follow up their implementation.
3. submit for approval by the regional government the structure of the Institute and its centers; follow up its implementation when approved.
4. approve the directives in which the personnel of the Institute will be administered.
5. review the annual work program and budget of the Institute and submit to the regional government for approval.
6. propose to the regional government the establishment of new research centers that represent different agroecological zones and farming systems that have a decisive role in the agricultural economic sector of the region and having potenial natural resources as deemed ncessary; evaluate and propose policy issues to the regional government for decision
7. establish a technical advisory committee, designate members of the committee and receive technical evaluation reports from the committee before approving budget for project proposals, projects and programs.
8. Evaluate the Regional Research, Extension and Farmer linkage Advisory Council; receive accomplishment report from the council.
9. Identify and propose for appointment, by the regional government, the Director General of the Institute, upon presentation by the President of the Regional State,
10. evaluate and present to the regional government researchers for award or incentives for meritorious achievements in agricultural research.

፬· የማዕከሉን የወደፊት አቅጣጫና ዕድገት በመተለም የሚያስፈልግ የማቴሪያልና የሰው ኃይል በማዘጋጀት ለዋና መሥሪያ ቤቱ ማቅረብ ፣

፭· በዋናው መሥሪያ ቤት በኩል በሚሰጠው መመሪያ መሠረት ሌሎች ተግባራትን ማከናወን ፣

፲፬· <u>የገቢ ምንጭ፣</u>

የኢንስቲትዩቱ በጀት ከሚከተሉት ምንጮች የተውጣጣ ይሆናል፡–

ሀ· በመንግሥት ከሚመደብለት በጀት ፣

ለ· ከምርምር ተረፈ ምርት ሽያጭና ከቤተ ሙከራ አገልግሎት ከሚገኝ ገቢ ፣

ሐ· ከማናቸውም ሌላ ምንጭ የሚገኝ ገቢ ፣

፲፭· <u>ስለሂሳብ መዝገብ</u>

፩· ኢንስቲትዩቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል ።

፪· ኢንስቲትዩቱ የሂሳብ መዛግብቱን በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰየመው ሌላ ኦዲተር እንዲመረመሩ ያደርጋል ።

፲፮· <u>ተፈጻሚነት የሌላቸው ሕጐች፣</u>

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ በዚህ አዋጅ ውስጥ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

፲፯· አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ ፣

ይህ አዋጅ ከኅዳር ፫ ቀን ፲፱፻፺፬ ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዋሣ ህዳር ፫ ቀን ፲፱፻፺፬ ዓ.ም.

ኃይለ ማርያም ደሳለኝ

የደቡብ ብሔሮች ፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል

ርዕሰ መስተድር

4. Submit to the head office the materail and manpower requiirements of the center based on its identified future direction and development needs.
5. Perform other functions based on the directives issued by the head office.

14. *Source of Income*
   1. The Institute shall have incomes from the following sources:
      a) budget allocated by the government
      b) laboratory service or sale of research by-products, and
      c) any other income obtained from other sources.

15. *Book of accounts*
   1. The Institute shall keep a complete and an accurate book of accounts, and
   2. the Institute book of accounts shall be audited by the Auditor General or by another auditor designated by him.

16. *Inapplicable Laws*

Any other laws which are in contradiction with this proclamation shall no be applicable with respect to matters provided for in this proclmation.

17. *Effective Date*

This proclamation shall enter into force as of the 12th day of November , 2001.

*Done at Awassa 12th Day of November, 2001.*

*HAILE MARAIAM DESALEGN*

*PRESIDENT OF THE SOUTHERN NATIONS, NATIONALITIES AND PEOPLES' REGIONAL STATE*

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE